የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 61
ADDIS ABABA, 12th July 2017

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፫/፪ሺ፱ ዓ.ም**

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በስሎቫክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ........................................................ገፅ ፱ሺ፯፻

**CONTENT**

Proclamation No.1033/2017

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Slovak Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification................................................page 9700

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፫/፪ሺ፱**

**በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት በታክስ ላይ የሚፈጸምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በስሎቫክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በስሎቫክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት መስከረም ፳፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፪ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

**PROCLAMATION No. 1033/2017**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLICOF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE SLOVAK REPUBLIC FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME**

**WHEREAS,** an Agreement for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income was signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Government of the Slovak Republic on the 1stday of October 2016, in Addis Ababa;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said agreement at its session held on 22nd June 2017;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በስሎቫክ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፴፫/፪ሺ፱ "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Slovak Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No.1033/2017".

**፪. የስምምነቱ መጽደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በስሎቫክ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል መስከረም ፳፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈጸምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Slovak Republic for the Avoidance of Double Taxation and the Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed on the 1st day of October 2016 is hereby ratified.

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በስራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to implement the Agreement in cooperation with the concerned government organs.

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**አዲስ አበባ ሰኔ ፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**Done at Addis Ababa, this 12th day of June 2017**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

REPUBLIC OF ETHIOPIA